## የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 882/2014 ማብራርያ

*መግቢያ*

በአገራችን ኢትዮጲያ የኮቪድ-19 ቫይረስ ከተከሰበት እና እየተስፋፋ ሲሄድ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማዉጣት እና አዋጁ መሰረት በማድረግ ደንብና መመሪያዎች በማዉጣት ዉጤታማ ስራ የተሰራ ሲሆን ቫይረሱ በአጭር ጊዜ በቁጥጥር ስር ማዋል የማይቻልና ለተራዘመ ጊዜ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መቆየት የሚያስከተለው ተጓዳኝ ጉዳት ታሳቢ በማድረግ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተነስቶ በመደበኛ ሕግ ተፈፃሚ እንዲሆን በተሰጠው ዉሳኔ መሰረት መደበኛ ሕጎቹ መሰረት በማድረግ ከወረሬሽኑ የስርጭት ደረጃ እና ባህሪ አንጻር በሽታዉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዝርዝር ክልከላዎችና ግዴታዎች የያዘ መመሪያ ቁጥር 30/2013 እና ይህን መመሪያ የሻረው መመሪያ ዉጥር 803/2014 ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የበሽታው ስርጭት አሁናዊ የስርጭት ደረጃ እና የበሽታው ክትባት መገኘት እና በአገራችን የክትባቱ አቅርቦት እና ስርጭት አበረታችና መንግስት በነፃ እየሰጠ ከመሆኑ አንፃር የነበሩትን የተወሰኑ ክልከላዎችና ግዴታዎች በማላላት ወይም በማስቀረት ይበልጥ ዉጤታማ የሚሆን የጥንቃቄ እርምጃዎችን ትኩረት የሚያደርግ አዲስ መመሪያ ማዉጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተዘጋጀ መመሪያ ነው፡፡

*የመመሪያው ዋና ዋና ድንጋጌዎች*

*መመሪያው በ 13 አንቀፆች የተዋቀረ ሲሆን አንቀፅ 1 የመመሪያው ስያሜ ፣ አንቀፅ ሁለት በመመሪያው ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት እና ሃረጋት ትርጉም እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡*

በመመሪው አንቀፅ 4 አጠቃላይ የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች በ 9 ንኡሳን አንቀፆች የተዘረዘረ ሆኖ በተለይ ከቤት ዉጪ ማስክ ማድረግ ግዴታ የነበረዉን ድንጋጌ በማስቀረት በተቋማት ፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፣ ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚገኙባቸው ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች ሊወስዱት የሚገባ የጥንቃቄ እርምጃዎች እና ክልከላዎች የያዘ ነው፡፡ በዚሁ አንቀፅ ክትባት የሚመለከቱ ድንጋጌዎችም ተካቷል፡፡

የመመሪያው አንቀፅ 5 በመግቢያና መዉጫ ስለሚደረግ የጤና ቁጥጥር የሚመለከት ሲሆን በስሩ 7 ንኡሳን አንቀፆች ይዟል፡፡ በዚህ አንቀፅ ማንኛዉም ወደ አገር ዉስጥ የሚገባ ተጓዥ ወደ አገር ለመግባት ማሟላት የለበት መስፈርት እንዲሁም መንገደኛዉ ያለ ምርመራ የሚገባበት ሁኔታም የያዘ ሲሆን በልዩነት መንገደኛዉ ዲፕሎማት ፣ ከስደት ተመላሽ ወይም ትራንዚት መንገደኛ ሲሆን በተለየ ሁኔታ እንዲታይ ተደርጓል፡፡

የመመሪያው አንቀፅ 6 እና 7 በስብሰባ እና በስፖርታዊ ወድድሮች ስለሚደረግ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚመለከቱ ሲሆን ቀድሞ በነበረው ከቤት ዉጪ ለሚደረግ መሰባሰብ ወይም ከቤት ዉጪ ለሚደረጉ ሁነቶች ተቀምጠው የነበሩ ክልከላዎች እንዲቀሩ ተደርጓል፡፡

የመመሪያው አንቀፅ 8 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስለ ግብረ-ሀይል መቋቋምና ስልጣንና ተግባሩ የመሳሰሉ ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በስልጣንና ተግባሩ የተወሰነ ማሻሻያ በማድረግና የተወሰኑ አዳዲስ የግብር ሀይሉ አባላት ከመጨመር ዉጪ ከነበረው ድንጋጌ ለዉጥ አልተደረገበትም

የመመሪያው የመጨረሻ አንቀፅ ልዩ ልዩ ድንጋጌ የያዘ ሆኖ ተቋማት ሰራተኞቻቸው የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ የማበረታት እና የማመቻቸት ኃላፊነት ከሚሰጠው የተጨመረ ድንጋጌ በስተቀር የነበረዉን የህጉ መተላለፍ የሚያስከትለው ቅጣት እና ሎሎች በዚሁ ክፍል የነበሩ ድንጋጌዎ እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡